ነሐሴ ፲፰ ቀን ፪ሺ፩ ዓ/ም

# የጀግኖችና የሊቃውንት ፉከራ

## ጀግኖች በነፍጣቸው ሊቃውንት በቅኔአቸው ይፎክራሉ!

(ከቀሲስ አስተርአየ)

በዘመናችን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነን እያሉ እያጳጳሱና እያመነኰሱ በሚልኳቸው ብቃት በሌላቸው ሰወች የነገረ መለኮቱ መዛባት እያሳዘነኝ ሳለ፥ ወንድሜ ዶ/ር ሥርግው ገላው "የፍልስፍናና የጥበብ መግለጫችን በማሕበራዊ ሕይወታችንም የጊስ መለዋወጫችንና የየግል ድካምና ብርታታችንን የምናይበት መስተዋታችን የሆነው የቅኔ ትምህርት እያሽቆለቆለ ይገኛል" ብሎ የተናገረውን በደጀ ሰላም ድኀረ ገጽ ላይ አነበብኩ:: አዎ! ቅኔ የፍልስፍናና የጥበብ መግለጫ ብቻ ሳይሆን፥ ነፍጥ የጀግኖች መፎከሪያ ጠላት መምቻና መገሰጫ እንደሆነ ሁሉ፥ ቅኔም መናፍቅና ከሀዲ ጳጳስ አላዊ መሪ (ንጉሥ) ሲነሳ ጠላትም አገር ሲወር የሕዝብ መቀስቀሻ፥ መፎከሪያ የጠላትና የመናፍቃን መንፈስ መስበሪያ ነበር::

**የጀግኖች ፉከራ፥** እናቶች የመረረ ግፍ ሲደርስባቸው ብሶታቸውን በልቅሶ ይገልጹታል:: ጥቃት የመረራቸው ጀግኖች አባቶቻችን ግን "ቤልጅጌ አለቀሰ ስቅስቅ ብሎ እንደ ሰው:: አልጋላይ ተኝቶ ቱሐን እየላሰው" ብለው ያላቸውን መሳሪያ ይዘው ከቤት ይወጣሉ:: የሕብረተ ሱቡን ልብ የሚአንቀሳቅሰውን ያካባቢ አየር ይቃኛሉ:: በተራራው በኮረብታው በቆላው በደጋው እየተዘዋወሩ በግፍ ክብደት ብሶቱን በመሬት ላይ ለመጻፍ አንገቱን ከደፋው ሕዝብ ጋራ በመስማማት ሐረጋቸውን የደፉትን እጸዋት ይመለከታሉ:: ከዚያ በኋላ "አማን ነው ዎይ? አገር አማን ነው ወይ" እያሉ ይሸልላሉ:: ያቅራራሉ:: "ቤልጅጉ ይጨኸ ጥይቱ ያልቅስ ቀለሁ ባሩዱ ይፍሰስ"እያሉ ፍፎክራሉ እንጅ ከእናቶቻቸው፥ ከሚስቶቻቸውና ከእኅቶቻቸው ጋር ቁጭ ብለው እራሳቸውን ይዘው አያለቅሱም::

**የሊቃውንት ፉከራ:-** ሊቃውንትም አገር ለተወለዱባት ልጆቿ የጋለ ብረት ምጣድ ስትሆን፥ ወንዶችን ሁሉ እየለበለበችና እየጠበሰች ቋንጣቸው መሽተት ሲጀምር፥ ሩጠው ማምለጥ የማይችሉ እናቶች፥ እርጉዞች፥ እኅቶች፥ ሕጻናትና ሽማግሎች በግፍ ሲጠበሱ ግፉን ለመቋቋም የሚጥሩ ጀግኖች ኃይል ሲአንሳቸው፥

"ሂጂ አገርሽ ግቢ ተመለሽ ቅኔ፥

ወንዶች በዋሉበት መዋሌ ነው እኔ"ብለው ቅኔያቸው በእንባቸው እያጀቡ ከየደብራቸው ይወጣሉ:: እንደ መምሕር ገብረ ኢየሱስ ከሕዝብ ጨፍጫፊ ጠላት እጅ መሳሪያ ነጥቀው ከተገፋው ሕዝብ ጎን ይሰለፋሉ:: ከጦር ሜዳ መልስም ለመቀደስ ወደ ቤተ መቅደስ አይገቡም:: ለሹመትና ሽልማት ወደ ቤተ መንግሥትም ዘወር ብለው አያዩም:: ይልቁንም ነቢዩ ዳዊት "ብጹዕ ብእሲ ዘኢሖረ በምክረ ረሲአ ወዘኢቆመ ውስተ መንበረ መስተሳልቅን" እንዳለው፥ በመንግሥት የሚዋቀረው ምክርቤት "ምክረ ረሲአን"ሲሆንባቸው መሪወቹ የተቀመጡበትን ኃላፊነት ረስተው በሕዝቡ ላይ በመሳለቅ ቤተ መንግሥቱን የመሳለቂያ መናሐሪያ ሲአደርጉትም ላለማየት ዓለም በቃኝ ብለው ይመንናሉ::

የተዋህዶው ነገረ መለኮት ሲቃወስ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱም እንደዛሬው ነገረ መለኮቱን ባላወቁ የከተማ ጮሌወች ስትወረር አባቶቻችን ሐዘናቸውንና ተግሳጻቸውን በቅኔአቸው ገልጸዋል:: የአንኮበሩ ታላቁ ሊቅ አለቃ ተክለ ጽዮን እንዲህ ብለው ነበር::

"በሰሚአ ቃሉ ለሳውል ቢጸ ኤርምያስ፥ ሰለስተ አክራመ ኢነትገ አንብዕነ::
ለዝኒ ብካይ ሀገረ ሳውል ኢኮነ::
ነግደ ወፈላሴ እስመ ሰብአ ቤቱ ለብካይ ንሕነ::
ቀዳሚ ጎበ ለመድነ፥ በላዕለ ብካይ ብካየ ወበላዕለ ኃዘን ኃዘነ::

**ለዓለም:-**

ሶበሰሂ ተዘከርናሃ ለደብረ ሊባኖስ እምነ::
ህየ ውስተ አፍላጋ ነበርነ ወበከይነ::
እስመ ማየ ዕድሜነ ሐልቀ ከመ ንዘረው ኩልነ::
መንፈቅነ ለምዕራብ ወመነገለ ምሥራቅ መንፈቅነ::"

ቅኔውን ከነ አገባቡ ጠንቅቀው አውቀው የምጻሕፍትን አንድምታ ተምረው፥ ምሥጢር አደላድለው ለቤተ ክርስ ቲያኒቱ ጠበቃ፥ ዋልታና ምሰሶ የነበሩ ሁሉ ሊቃውንት እንደዛሬው ተዋርደው ተሰደውና በሞራል ዘመቻ ተደርጎባቸው በነበረበት ዘመን አለቃ ሲራክ የተባሉት የዋድላው ሊቅም ::

"አዕዱግ ወበቅል እንዘ ያወጽኡ ስሳ፥
ሲራክ አምላከ ዋድላ ተሰይጠ ሰላሳ" ብለው ነበር::

ለሰንበት አስተማሪነት በአጫጭር ኮርስ ለሁለትና ለሶስት አመታት የሰለጠኑት የሰንበት ተማሪወች፥ ሊቃውንቱ ይናገሩ መጻሕፍት ይመስክሩ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ይፍረዱ ከማለት ይልቅ፥ ባልዋሉበት ባልደከሙበትና ባልተረዱት ነገረ መለኮት ውስጥ በመግባትና ለሚአገኙት ጥቅም ብቻ ሲሉ እራሳቸውን መምሕር እያሉ በመሰየም፥ በቴፕ ካሴት እየቀረጹ የሚያሰራጩት ስብከትና መዝሙር ከኦቶዶክስ ተዋሕዶ ነገረ መለኮት ቅርጽና ይዘት የወጣ፥ ከባእድ እምነት ጋራ የተቀየጠ ነው:: በተዋሕዶው ነገረ መለኮት ተመዝኖና ተቀምሮ ሲዘመር የነበረውን ያስለቀቀ፥ የስነ ጽሑፋችንን ለዛ ያስናቀ፥ ከተዋሕዶው ነገረ መለኮት ፈጽሞ የራቀ  መዝሙር በማሰራጨት ላይ ያሉ ሰርጎ ገቦች ዛሬ በሊቃውንቱ ላይ እንደዘመቱ ሁሉ፥ ከኛ በፊት በነበሩት ሊቃውንት አባቶቻችን ዘመንም ፊደል የቆጠረ ሁሉ አዋቂ ነኝ ብሎ በመሰለፍ ሊቃውንቱን አሳደዋቸው ስለነበረ ለዚያ ዘመን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ እንዲህ ብለውም ነበር::
"መምህራነ ኮኑ በበደውሉ፥
ፊደላተ ዘኖለቁ ኩሉ"

እንደ ዛሬው የውጭ እምነት ወደኛዋ ቤተ ጅርስቲያ ሰርጎ ሊገባ በቃጣበት ዘመን እነ መላከ ኃይል ተድላ በተዋህዶው ነገረ መለኮት ማሽነፋቸውን ለመግለጽ
ከነሱ በኋላ ለምንከተላቸው ለኛ ከዚህ በታች የሰፈረውን ቅኔ ለታሪክ ትዝታ ትተውልንም ነበር::

**ለዓለም:-**

"ከንቶ ነገረ አመተናገሩ፥ ሰብአ ሮምያ አጽራር: ኢይከውን ለቅያሜ፥
በባሕለ ነገሮሙ ሮም እንተ አልባቲ ፍጻሜ፥
እስመ አብደ ሕሊና ልቦሙ ወኮነ ሐማሜ
ወየብሰ እምልምላሜ ጽጌ ሃይማኖቱ ምጽልው ዘተዘርዎ ከመ ጊሜ፥
ኢትበልሂ ወላዲሁ በተቀብአ ንባብ አበሜ፥
ዮሴፍ ለቃለ አብ እንተ የአቅቦ ምስለ ሰሎሜ፥
ርኢናሁ ለበትር እንዘ ይጌስጻ ለሮሜ፥
ቅሩጸ በንባብ ወጽሩበ በትርጓሜ"

እምነት ሲደበላለቅ፥ በሕዝቡ ኑሮ ላይ የሚኮሰኩስና የመንፈስን ስሜት የሚአንቅ የሚኮሰኩስ ምርቅ ሲከሰከስበት በቤተ መቅደስና በቅድስት ቆመው የሚአነቡ ሊቃውንትም በጧት እየተነሱ "አድኀን እግዚኦ ዘተኒ ሀገረ ወካልዕታኒ አህጉረ ወበሐውርተ እለ በሃይማኖተ ዚአከ የኀድሩ ውስቴቶን ቅዱሳነ አድኀን እምልቅልቅ ወእምረኃብ ወእመራደ ካልዕ ሕዝብ" ( ሊጦን ዘነግህ) በማለት ከመንፈሳቸው መነጭቶ ልባቸውንና አንጀታቸውን የሚአንሰፈስፍ ልቅሶ ያለቅሱ ነበር:: በጾም በስግደት ይበረቱ ነበር:: እንደ ዛሬወቹ ካህናት እኔንም ጨምሮ መወፈርና መቅላት መውዛት ይቅርና፥ ጠቁረው ቀጭጨውና ጠውልገው ይታዩ ነበር::

ካህናት በቅኔያችን ከበሰሉ፥ በነገረ መለኮቱም ከረቀቁ ሕዝቡ ከስቶ እነሱ እንዳልተፈተገ ገብስ አይወፍሩም:: ካህን በቅኔ ካልታሸ በነገረ መለኮቱት ምሥጢር ጭንቅላቱ ካለፋ፥ "ጠላሽ በቀጠነ ዳቦሽ ባረረ ይቀበለው እግዚአብሔር አቡነ ዘበሰማያት" ከማለት በቀር የሕዝቡ መጎሳቆል፥ የነገረ መለኮቱ መበከል አይሰማውም:: አባቶቻችን እንኳን ሊሰማው "የጨው ካብ ሲናድ ሞኝ ይልሳል፥ ብልህ ያለቅሳል" እንዲሉ፥ ለግሪን ካርድ፥ ለብር፥ ለተደላደለ ኑሮ፥ የሚአስብ በሕዝቡ የተገመተ ደካማ ሞኝ ይሆናል:: ቅዳሴውንም መተዳደሪያና ጥቅም ማግኛ ያደርገዋል:: ሙቀጫ ያላሸው ገብስ እንጀራም ቆሎም አይሆንም፥ በውሐ ተነክሮ መወቀጥና መፈተግ፥ መነፋት ለጸሐይ ተዘርሮ መሰጣት አለበት:: "ቅኔ ያልተማረ ቄስ ሙቀጫ ያላሸው ገብስ" አንድነው እያሉ የቀደሙ አባቶቻችን ሊቃውንት ይናገሩ የነበረ፥ ከነሱ ቀጥለን በአገራችን የምንፈጠር እኛ ካህናት እንዲህ እንደዛሬው የተሽመደመደ መንፈስ እንዳይፈጠርብን ነበር::

ይቅርታ ይህን ስል፥ የቀደሙ አባቶች ሲታገሉት የነበረውን የሮማ ካቶሊኮችን እምነት፥ ቤተ ክርስቲያን ወክላኛለች እያሉ በሚአጭበረብሩ እንደ አባ ማትያስ ያሉ የራሳችን ሰወች ሌላውን ሁሉ ሲለቀልቁ ኖረው እኔ ካለሁበት ቦታ በማድረሳቸው ከሁሉም በበለጠ ሁኔታ ሰለተሰማኝ እንጅ፥ ከማነኛውም የተሻልኩ ነኝ ማለቴ አይደለም:: ከላይ ከተገለጹት ሊቃውንትና አርበኞች አባቶቼ የሚአወዳድረኝ እውቀትም ወኔም ችሎታም የለኝም::

ይሁን እንጅ በቅዳሴአችን ላይ "ንሑር በፍናዊሆሙ ወንትሉ በአሰሮሙ ወንትመሰል ኪያሆሙ" የምንለውን በማስታወስ አባቶቻችን በጮሁበት ቅኔ ስለነገረ መለኮቱ ለመጮህ አባቶች በውስጤ ያስቀመጡትን ያደራ ቃል ላማሰማት ትኀትና የሚጠይቅ ሆኖ አላገኘሁትም:: አባቶቻችን በዘመናቸው በኢትዮጵያ የደረሰው ጉዳት፥ በቤተ ክርስቲያናቸውም የደረሰው ጥፋት አሳዝኗቸውና አስቆጥቷቸው የፎከሩባቸውንና የገሰጹባቸውን ቅኔወቻቸውን እንደአብነት በመከተል፥ እኔም በዘመኔ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናች የገባው ስሕተት ያስጮኹኝን ለመግለጽ ከዚህ ቀጥየ በማቀርባቸው ቅኔወቼ የጮኹቴን ድምጽ አቅርቤአለሁ:: ::

**፩ኛ ሚበዝኁ:-** "እግዚኦ ሚበዝኁ እለ ይሣቅዩኒ"

ለሐራሴ ምድር ማትያስ: ንግርዎ ያዕምር: መጽሐፈ ብሉይ ወሐዲስ::
ከመ በስሕተት ኢይፍጽም አፈ ብራዕዩ ቀሲስ::
በውስተ ኦርቶዶክስ አውድ: በጊዜ ያከይድ: እክለ ትርጓሜ መጽሐፍ ቅዱስ::

**፪ኛ ሥላሴ:-** "ይትባረከ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ"

እንከ እምነዮም: ኢንሰቲ ንሕነ:
ስቴ አበው፥ ምሥጢረ ሃይማኖት ርትዕት እንተ በስቴሁ ልሕቅነ::
ሊቃውንት መሳብክተ ቤት እስመ ሐልቁ ብነ፥
ወአጺረ ወይን አጽርአት፥ በቤታ ቤተ ክርስቲያን እምነ:
አኮኑ ዘተርፉ ልሁክታቲነ
አስግሩ ለነ ቆናለ ንኡሳነ
እለ ያማስኑ አጸደ ወይንነ::

**፩ኛ መወድስ:-** "ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልዬ"

እመ በኩሉ ተሰርአ ሥርአተ ክሌቱ፥ ለአንደበራ ማትያስ
ናስተማስሎ በይነ ምንት::
ንመስሎኑ በይስሐቅ ወበእስማኤል ምውት:
ዘተወልደ በአመጻ፥ እምአጋር እቤርተ ቫቲካን እሙሐይ ብርጂት:
ወእንበለ ምሕረት አገቱኒ በአፍአ ወውስጥ ማኅበረ ሌጊዮን ከለባት፥

**ለዓለም:-**

አመ ጸንአሂ ወተኀየለ እንተ መስቴማ ሕውከት፥
ማትያስ ውስተ ሮሜ ወአንሰ በናዝሬት፥
ወእፎ እኩይ ዘመነ ትውልድ እሉት:
እስመ ጣዕዋ ኀበ መርኅብ፥ ወአድኀ መርኅብ ኀበ ቤት::

**፪ኛ መወድስ:-**

በሐመልማለ ሐቅል ማትያስ በዓለ ዘመን፥ ተደሙ ጥቀ
ኦርቶዶክሳውያን ዘዓለም::
ለዕብነ አድማስ ደቅ ኮኩኀ ሃይማኖት ፍጹም፥
እንዘ ይሰብሮ ወይገድፎ፥ ርእይዎ አኮኑ በቆጽሉ ጽሒም፥
ወበ ሲኖዶስ ዘካርያስ፥ ተደሙ ጥቀ አምጣነ ልሣኑ በሐም፥

**ለዓለም:-**

በከንሳስሂ አመ ተሰማአ ገአረ ማትያስ ሎም
ተጋብኡ ሌጌዮን ቆናጽለ ሐቅል ወገዳም፥
አኮኑ ፈተው ለበሊአ ሥጋ ወአጽም::
ወእስከ ይህዝ ያነክስ ማትያስ ዝሕበ ገደም

**፫ኛመወድስ:**ከመጽሐፈ መሳፍንት ምዕ ፲፱ የተወሰደ ነው::

ቤተ ክርስቲያን ልዕልት መራተ ሌዋዊ፥ ዘበዘባና ተነጽሐት በኍኖኅተ አዝማድ ዘኖሙ፥
ኢክሕለት ትቁም በከመ ልማዳ ቀዲሙ፥
እስመ ወድቁ በላዕሌሃ፥ ወተዋነይዋ ብዙኃን ኩሎሙ፥
ሠራዊተ ሌጊዮን ኃጥአን፥ ወደቂቀ ማኒ ወፒዮስ እለ በኑፋቄ
ያስተቃስሙ::

**ለዓለም:-**

ምእመናንሂ ዘከንሳስ እስራኤላውያን ቆሙ፥
ለገረ ፍትሕ ይትቀሐው በጥቡዕ ልቡናሆሙ፥
ወእምትይንቶሙ መጽኡ አዝማደ አኀቲ እሞሙ፥
ዘተመትረ ኩለንታሃ እስመ ተፈነወ ኀቤሆሙ፥

ባጠቃላይ ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ያብነቱን ትምህርት ተምረናል የምንል ሁሉ: ዛሬ የተፈተንበት ወቅት ነው:: እምነቱ በተቃወሰበት አገሪቷ በተናወጠችበት፥ የሲኖዶሱ አባላት ነን የሚሉ ሁሉ ከመንፈሳዊው ዓለም ወጥተው በሙስና ተዘፍቀው እርስ በርሳቸው በሚናኅዱበት ወቅት፥ ያልተማሩ በጉባዔ ትምህት ቤታችን ያልደከሙ የሰንበት ተማሪወች ሕዝቡን በክህደት ትምህርት ሲአምሱት አፍን ለጉሞ፥ እንዳላዩና እንዳልሰሙ መስሎ መቀመጥ ባወቀውና በተረዳው ሕዝብ ፊት አስነዋሪና አስተዛዛቢ ነው::

ክህነታችንን ሳንቲም መሰብሰቢያና ግሪን ካርድ ማውጫ ለማድረግ የምናሳየውን ትጋትና ጥበብ፥ የተዋሕዶውን እምነት መጠበቂያ የሕዝቡን ድምጽ ማስተጋቢያ በማድረግ እንጠቀምበት:: እመቤታችንን ከሰው ውጭ ከሚአደርጋት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከምታስተምረው ከ"Immaculate Conception" ውጡ:: በቅኔአችን በቅዳሴአችን

በወንጌላችን ሁሉ የኦርቶዶክሱን ነገረ መለኮት በመከተል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ተረዷት፥ እወቋትም:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዶግማ አትቀበለውም:: አባቶቻችን በዘመናቸው ከነሱ የተሰነዘረባቸውን ወረራ የተቋቋሙት እመቤታችን "የተዋረዱትን የጎሰቆሉትን፥ ከፍ አደረጋቸው:: የተራቡትን በበረከቱ አጠገባቸው:: ትቢተኞችን ራቂታቸውን አቆማቸው" ብላ ጮሓ የተናገረቻውን የነጻነት ድምጿ ምሳሌ በማድረግ ነው:: ከሴቶች ልማድ የተለየች፥ ከኪሩቤልም በላይ ብትሆንም የአዳም፥ የኢያቄምና የሐና ልጅ በመሆኗ "እኅትነ ዘመድነ" እያሉ ያወድሷታል እንጅ አሁን በዘመናችን ቤተ ክርስቲያኒቱን በወረሯት የሰንበት ተማሪወች መንገድ አባቶች አይገልጿትም ነውር ነው ክህደት ነው ጸያፍም ነው::

አባቶቻችን እንደ **ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም**፥ በቅኔያቸው ከተዋረደውና ከተጎዳው ሕዝብ ጋራ በመሰለፍ እየተቀኙ አልፈዋል:: እኛም እንደ እመቤታችንንና አባቶቻችን ሊቃውንት ከራሳችን ክብርና ጥቅም ተላቀን ከተጎዳውና ከጎሰቆለው ሕዝብ ጋር በመሰለፍ በቅኔያችን በቅዳሴአችንና በወንጌላችን ብሶቱን እንቀኝ:: ይልቁንም እውጭ የምንገኝ ካህናት ላልተረዳውና ለሚመለከተው ለማሳወቅ እውስጥ ታፍነው ከተያዙት ሊቃውንት አባቶቻችንና ወንድሞቻችን የበለጠ ሐላፊነት ይጠበቅብናል:: ለዚህ የሚአበቃ የመንፈስ ጥንካሬ፥ ለጾምና ለጸሎት የሚያተጋ ልቡና ኃያሉ እግዚአብሔር እንዳይነፍገን የዘወትር ጸሎቴ ነው::

ስለ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም እመቤታችን የጥንት ኦርቶዶክስ ሊቃውንት አባቶቻችን እንዴት እንደገለጿት ግልጽ በሆነ መንገድ ገልጨ በማቀርበው ጽሁፌ እንገናኝ::

**ይቆየን::**

nigatuasteraye@yahoo.com